## ጥያቄ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ጥቅሶች መሰረት **ምን ማድረግ አለብን?**
## የተባልነውን ስናደርግስ **ምን የመሆን ስልጣን እናገኛለን?**

"**ለተቀበሉት** ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ **የእግዚአብሄር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው**" የሐ 1፤12
"የጌታ ስም **የሚጠራ** ሁሉ **ይድናል**" ሮሜ10፤13
"**ልጁ** ያለው **ህይወት** አለው፤ **የአግዚያአብሄር ልጅ የሌለው ህይወት የለውም**
"**የዘላለም ህይወት** እንዳላችሁ **ታውቁ** ዘንድ" የሐ 5፤12-13




# እየሱስ እንዲህ አለ

" እኔ የዘላለም ህይወት እሰጣችኃለሁ
ለዘላለምም አይጠፋም " ዮሐ10፤28

# ምርጫው ያንተ ነው!

## ይህን ጸሎት በእምነት ከልብህ በመጸለይ ክርስቶስን በመጋብዝ የዘላለም ህይወትን አሁኑኑ በነፃ ተቀበል!

**ሁሉን ቻይ የሆንክ አምላክ ሆይ በሀሳቤ ፣ በቃሌና በድርጊት በድየሃለሁ ፤ ማረኝ ከእየሱስ ክርስቶስ ምህረትን መቀበል እፈልጋለው ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ሆይ አዳኜና አምላኬ አድርጌህ እቀበልሀለው ከሃጥያቴና ከዘላለም ፍርድ አድነኝ የዘላለም ህይወት ስጠኝ ለዘላለም አዳኜ ወዳጄና አምላኬ እንድትሆን ወደ ህይወቴ እጋብዝሃለው::**

**ፊረማ --------------------** **ቀን --------------------**

**እየሱስ እንዲህ አለ "እኔ የዘላለም ህይወት እሰጣችኃለሁ ለዘላለምም አይጠፋም " ዮሐ10፤28**

**ጥያቄ 1** **ከሀጥያትህ እንዲያድንህ እየሱስ ክርስቶስን ጠርተህዋል? ጠሎትህስ በእውነት ከልብህ ነው ?**
**እግዚአብሐር በሮሜ10፤13 መሰረት ምን ትሆናለህ ይላል? ከምንድነው የሚያድንህ ?**
**ድንገት በዚህ ሰአት ብትሞት ነፍስህ ወዴት እንደምትሄድ አውቀሃል? ለምን?**

**ከዳንክ በኃላ የዘላለም ህይወት የምታጣበት ምክንት ይኖራል? ዮሐ10 ፣ 28 ተመልከት**
**"ለዘላለም አይጠፋም" ሲል ምን ማለት ነው? እየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር**
**እግዚአብሄር ከሙታን እንዳስነሳ ከልብህ ብታምን ትድናልህ (ሮሜ10፣ 9)**

**ጥያቄ 2** **እግዚአብሐርን በበለጠ ለማወቅ ምን ማድረግ አለብህ?**

- **ዘወትር መጽሃፍ ቅዱስ ማጥናትእግዚአብሐርን በበለመ እንድታውቅ ይረዳሃል (1ጴጥሮስ 2፣2)**
- **ጸልይ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የምትሰጥ ቤተክርስቲያንን ተከታተል (ዕብ10፣24-25)**
- **ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ለሌሎች ሰዎች መስክር**
- **የውሃ ጥምቀት ተጠመቅ (የሐዋ10 ፣ 47-48)**
- **መዳንህን ለሌሎች መስክር (ሮሜ10 ፣ 9)**
- **ለክርስቶስ አየታዘዝክ ኑር**

**'' የዘላለም መኖርያህ የት ነው '' ?**

# ቆም

## ብለህ አስብበት!

የማያልቅ ህይወት እንዴት በደስታ እንደሚኖር




# የዘላለም ሕይወትን ከእግዚአብሔር **በነጻ** ተቀበል!

# **የዘላለም ሕይወት አለህ?**

## ኢየሱስ ክርስቶስ በማንነቱና ለእኛ በፈጸመው ሥራ እጅግ ታላቅ ዋጋ አለው።

1. ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ነው። ዩኒቨርስ፣ ሰው፣ እንስሳት፣አ ጵዋት፣ ለሕይወት አስፈላጊ የሆነ በሙሉና ... ወዘተ በእርሱ ተፈጥሯል። "**ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም**" **ዮሐ**፡ 1፤3
2. ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አንድነት ሶስትነት (ምስጢረ ሥላሴ ) - **አብ፣ ወልድ** (**የግሪክ ቃሉ ሁዊያስ**) **እና መንፈስ ቅዱስን ገለጠ። ማቲ** 28 ፡ 19 ፤ **1ኛ ዮሐንስ** 5 - 7
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹**በስጋ የተገለጠ**›› (1**ጢም** 3፤16) ‹‹**ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛ አደረ..**›› (**ዮሐ** 1፡14) የሚል ምስጢረ ስጋዌ (ትስጉት) ነው።
4. እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ (**ቆላስያስ** 1፡15፤ **ዕብ** 1፡39 2 **ቆሮ** 4፡4) የመለኮታዊ ባህሪያትና ሰብዓዊ ባህሪያት የጋራ (interface) ወይም **ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው** የሆነ ስብዕና ማለት ነው።
5. 45 የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች በሕይወቱና በሕማማቱ ስለተፈጸሙ መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥ የእግዚአብሐር መሆኑን አረጋግጧል። **ኢሳ** 41፡23
6. **በሉቃስ** 21፡20-24 ስለ ኢየሩሳሌም፣ ቤተመቅደሱ፣ የአይሁዶች መበተንና የኢየሩሳሌምን ከተማ መጣት የተነበየው ትንቢት በሙሉ ተፈጽሟል።
7. ክርስቶስ ስለ ኃጢያታችን መከራ ተቀብሎ ሞተ፣ ተስቅሎ በመሞቱም ለእኛ ኃጢያት ማስተሰሪያ በቂ መስዋዕት በማቅረብ የእግ/ርን ህግና ፍትህ ሳይጥስ መለኮታዊ ፍቅሩን ገልጧል።
8. ክርስቶስ ሞትን ድል ነስቶ ከሙታን በስጋ በመነሳቱ በእርሱ የሚያምኑትንም እንዲሁ ከሙታን ያስነሳቸዋል። ይህ የትንሳኤው ኃይል ባዕድ አምልኮን ሁሉ ከንቱ አድርጎአቸዋል።
9. በኃጢያታችን ምክንያት ህጉ የፈረደብንን ሞት ሽሮ የሞትንም ፍርሃት አስወግዶ የዘለዓለም ሕይወት ሰጥቶናል።
10. ሊያጽናናን፣ ክርስቲያናዊ ኑሮንና የዳግሞ ምጽዓቱን ትዕይንቶች ሊያስተምረን አዲስ ኪዳን ሰጥቶናል።
11. ከእግዚአብሔር ጋር መለኮታዊ ፍቅር ላይ የተሰመረተ **ሰላማዊ ወዳጅነት** እንዲኖረን አድርጓል። ወዳጆች ... ብያችኋለሁ›› ዮሐ 15፡15
12. ክርስቶስ፣ በፍትህና በነጻነት የሚኖር፣ ለሰው ሕይወት ክብር ያለው ሰላማዊ ማህበረሰብ እንዲኖረን ያደርጋል።
13. ለክርስቲያናዊ አገልግሎቶቻችን ሽልማቶችን ይሰጠናል። «**ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነው።**» **ማቴ** 5፡12
14. በመከራችን መጽናናትን ለችግሮቻችን መፍትሔዎችን ይሰጠናል። «**በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር**» **የሐዋ** 9፡31
15. እግዚአብሔርንና ሰዎችን መውደድ ያስተምረናል። « **እንደወደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ** ...» **ዮሐ** 13 ፡ 34፤35
16. አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ በመነጋገር እንድንፈታ ያስተምረናል። ማቴ 18፡15
17. እውነት፣ ጥበብ፣ ፍቅር፣ ደስታና ሰላማዊ ኑሮን ያስተምረናል። «**ሰላሜን እሰጣችኋለሁ**» **ዮሐ** 14፡27
18. ነጻ ገበያን ይደግፋል፤ የኮሚውኒዝም ስርዓትን ይቃወማል። «**ምናንህ አስር ምናን አተረፈ**» **ሉቃ** 19፡16
19. የህዝብ መሪዎችን እንደህዝብ አገልጋዮች እንጂ እንደ አምባገነኖች አልገለፃቸውም። ማር 10፡ 42-45
20. ሆስፒታሎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና የመጽሐፍ ቅዱስ ማተሚያ ድርጅቶች እንዲሰሩ ምክንያት ( Inspire ) ሆኗል።
21. ክፋትን ሁሉ አስወግዶ **የሺ ዓመት መንግስቱን** ለማቋቋም ወደዚህ ዓለም ተመልሶ እንደሚመጣ የ ተስፋ ቃል ሰጥቶናል። ማቴ 25፡ 31-46

**የዘላለም ሕይወት እንዳለን እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን?**

# የሚከተሉትን 4 ነገሮች ማወቅ አለብን።







ኃጢአት ማለት መለኮታዊ ህግ መተላለፍ ማለት ነው።


## 1. ሁሉም ኃጢአት ሰርቷል።

**‹‹ሁሉ ኃጥአትን ሰርቷልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤›› (ሮሜ 3፡23)**


**ኃጥኢት ማለት ምን ማለት ነው?**




ራስ ወዳድነት




ከእግዚአብሔር መለየት




በመለኮታዊ መመዘኛ ሁሉም ወድቆአል

**በእግዚአብሔር የቅድስና መለኪያ ስንታይ ሁላችንም እጅግ በደለኞች መሆናችንን እንረዳለን።**

ጥያቄ 1፡- በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው አምላክ አምላክህ እንዲሆን ትወዳለህ?

ጥያቄ 2፡- ንስሀ በመግባት ወደ እግዚአብሔር መመለስ ትፈልጋለህ ?

## 2. ኃጢአት የሚያስከፍለው ዋጋ ሞት ነው?

**‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና ፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።** (ሮሜ 6፡23)

**‹‹ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። ››** (ራዕይ 20፡14)

**ማብራሪያ፡-** ለኃጥያታችን ቅጣት የሚሆን የሞትና የእሳት ባህር ዘላለማዊ ፍርድ እንደሚጠብቀን የእግዚአብሔር ህግ ደንግጓል። በመሰረቱ የእሳተ ባሕር የተዘጋጀው ኃጥኢታዊ ባህሪን ለመረጠው ሰይጣን ነበር። ወደዚህ ፍርድ መምጣት የሚፈልግ ማንም ሰው የለም።

ከዚህ ፍርድ የማምለጫ መንገድ ይኖር ይሆን? በእርግጥ አለ! እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን በክርስቶስ አማካኝነት እንዲያው በነጻ ይሰጠናል። በግል ጥረታችን (በመልካም ስራችን) ወይም በሃይማኖት ድርጅቶቻችን ፈጽሞ የዘላለም ሕይወት ማግኘት አንችልም።

**ሞት ማለት**



የሥጋ ወደ አፈር መለለስ







**‹‹ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም››** ኤፍሶን 2 8-9

**ስጦታ፡-** ገጸበረከት ነው ፤ መቀበል ወይም መተው ይቻላል።

**የዘላለም ሕይወት፡-** አሁን እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ከሞት በኋላ ደግሞ በመንግስተ ሰማያት ከእርሱ ጋር የማያልቅ ሕይወት በደስታ መኖር ማለት ነው።


ስለዚህ በሁለት ጎታች ሀይሎች መሀል ነው ተጠምደን ያለነው፡ መለኮታዊ ህግና መለኮታዊ ፍቅር ፡፡
የእሳት ባህር ፍርድ እንደሚገባን ሲነግረን የእግዚአብሔር ፍቅር ደግሞ ወደ መንግስተ ሰማያት ሊወስደን ይሻል።

እግዚአብሔር ይህን ችግር እንዴት ፈትቶ የዘላለም ህይወት ይሰጠናል ?

በሥጋ ተገልጦ ፍፁም ሰው ሆኖ ለኛ ኃጢአት መስዋዕት በማቅረብ ነው።

## 3. ኢየሱስ የኛ ምትክ ሆኖ የኃጢያታችንን ዋጋ በሙሉ ከፈለ።

**ነገር ግን ኃጥያተኞች ስላለን ክርስቶስ ስለኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።** ሮሜ 5-8




ለኃጥተኞች ምትክ ሆኖ በመሞቱ ክርስቶስ
የሰው ሁሉ **አዳኝ** ነው።
እሱ ከኃጥያትና ከሞት **ሊያድንህ ዝግጁ** ነው።

**ማብራሪያ** እግዚአብሔር **ያለብንን** ኃጥያት በሙሉ (አላፈውም፣ የአሁኑን እና የመጪውን ሁሉ) **በክርስቶስ** ላይ አኖረ

እኛ ሁላችን እንደበጎች **ተቅበዝብዘን** ጠፋን ፤ ከእኛ እያንዳንዱ **ወደ ገዛ መንገዱ** አዘነበለ ፤
እግዚአብሔርም የሁላችን **በደል በእርሱ ላይ አኖረ።**
ኢሳያስ 53 - 6

**ከእሳት ባህር ፍርድ ሊያድነን ኢየሱስ ምትካችን ሆኖ የኃጥያታችንን ሙሉ ቅጣት በመሸከም በመስቀል ላይ ሞተ።**

እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለበደላችንም ደቀቀ፣ የደህንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን ። ኢሳያስ 5-13

ክርስቶስ የሰው ሁሉ **አዳኝ** ( የኃጥያታቸው ቅጣት ያረፈበት ) ነው። የመንግስተ ሰማያት ደጅ **ለሁሉም** ሰው ተከፍቷል። ስለዚህ ወደ መንግስተ ሰማያት **እንዴት** መግባት እንችላለን?

### የሚከተለውን የሚያምኑ ምህረትና የዘላለምን ህይወት በነፃ ያገኛሉ

## 4 . (ሀ) እየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው መሆኑን የሚያምኑ

- እግዚአብሔር ወልድ መሆኑን የሚያምኑ
- የኛ ምትክ ሆኖ ስለኃጥያታችን እንደሞተ የሚያምኑ
- በሥጋ ከሙታን እንደተነሳ የሚያምኑ

## (ለ) እየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝ አድርጎ የሚቀበሉ።

ይህ ማለት የዘላለም ህይወትን ለመቀበል በቀራንዮ መስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ብቻ ለኃጥያታችን በቂ ማስተሰርያ መሆኑን መቀበል ማለት ነው።









እግዚአብሔር በገባልን **የተስፋ ቃሎች** ላይ **ሙሉ እምነታችንን በመጣል**
የዘላለም ሕይወት እንደተቀበልን መቶ በመቶ ዛሬውኑ **እርግጠኞች መሆን እንችላለን**